# ለኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ለጸጋዬ ገብረ-መድህን ትዝታ

(ከእሸቱ ጫቦ)

ድሩንና ማጉን ይዞ ኢትዮጵያን ሊሸምን፣
የዶርዜ ጥበቡን ሰራና ሰራና፣
ቁጭትና ቁጪት ትቶልን አረገ፣
ሞትም አብሮት ሞተ ቶሎ ተሸቀዳድሞት፣
በዕይታው ብርሃን ባውዛውን ለቆበት።

የማህሌት አባት፣ የሴንጎር ወንድም፣
የሺክ አንታዲዮፕ፣ የነፍሬ ሊሞ፣
ፍሪ - ደም እያሉ፣ ፍሪደም ለሚሹ፣
ወዶ ድንቁርና፣ ወንጀል ነው እያለ፣
የፍሬውን ፍሬ በማህሌት ውዳሴ ማን አየበት ብሎ፣
የስነ-ቋንቋውን መሰረት አስልቶ፣
ፈረንሳይ አይሆንም ውልፍ ነው እንጅ፣
አንደበተ-ሴንጎር እንዲሁም ሴኔጋል፣
መክሮ አስቀይሮ፣ ዘረኛ አሳብዶ፣
ዓለም ኢትዮጵያ ነች፣ ኢትዮጵያም ዓለም።

በትንሽ በትንሽ ይድረስ ለወንድሜ፣
ለማላውቅህ ብሎ፣
እንዲንተዋወቅ ዓለም ሊያቀራርብ፣
የታየው ታይቶት ነው፣
በቃኝ ልሂድ ያለው፣
ሞት እንጅ የሞተው፣ ጸጋዬ ሕያው ነው፣
ጸጋዬ ፀጋዬ ጸጋዬ አይሞትም፣
አቦ ማህሌት፣
ብርሃን መች ይጠፋል፣
ጨለማ ይስጋ እንጅ!!

ለማንኛውም አድራሻዬ፡ addisminch@hotmail.co.uk ነው።